


# ምስጢረ ሥላሴ MYSTERY OF TRINITY

# ሥላሴ
## (Trinity)

- "**ሥላሴ**" የሚለው ቃል "ሠለሰ" ሦስት አደረገ ካለው የግዕዝ ግሥ የተገኘ ሲሆን ሦስትነት ማለት ነው፡፡
- ***ቅድስት ሥላሴ*** ማለት ልዩ ሦስትነት ማለት ነው፡፡
- **ልዩ ሦስትነት**: ሦስት ሲሆን አንድ፣ አንድ ሲሆኑ ሦስት (ልዩ ሦስትነትን ማመንን ፈጽምልን (ጸሎተ ቡራኬ))
- የአንጾኪያው ቴዎፍሎስ በ169ዓ.ም ጽፎታል፡፡

- The word '**Trinity**' means a group of three things or people.
- Refers to the existence of one God in three Persons
- Holy Trinity: Three in One, One in Three.
- First used by *Theophilus* of Antioch (169 AD) to explain eternally existing reality.

# ምስጢረ ሥላሴ
## (Mystery of Holy Trinity)

- የክርስትና ዶግማ (መሠረተ እምነት) በምስጢረ ሥላሴ ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ ለመዳናችንም መሠረት ነው፡፡
- ሁላችን የተጠመቅነው በሥላሴ (በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ) ስም ነው፡፡ ማቴ 28፡19
- የሥራችን ሁሉ መጀመሪያም አድርገን በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ስንል በሥላሴ ማመናችንን እየመሰከርን ነው፡፡
- በመጨረሻም "ምስጋና ይሁን አንድ አምላክ ለሚሆን ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ…" እንላለን፡፡

- The most Fundamental of all Christian dogmas. It's the basis for our salvation.
- We all are Baptised in the name of Trinity: The Father, the Son and Holy Spirit. Matt 28:19
- We start our prayer or other spiritual services 'in the name of the Father, of the Son, of the Holy Spirit'
- At the end, we say "Glory be to the Father, the Son, the Holy Spirit…"

# አንድ አምላክ፣ ሦስት አካላት
## (One God, Three persons)

**አንድነት**

በባሕርይ፣ በመለኮት(በአምላክነት)፣ በሕልውና፣ በፈቃድ፣ በፈጣሪነት፣ በአገዛዝ፣ በሥልጣን

(ዘዳ 6፡4 ኢሳ 44፡6 ኢሳ 43፡1 ዮሐ 10፡30)

**ሦስትነት**

በአካል፣ በስም፣ በግብር

(ማቴ 28፡19 1ኛ ቆሮ 12፡4-6 ሮሜ 14፡17)

**ONE**

Essence/Nature, Divinity, Power, Action, Will

(Deut 6:4, Isai 44:6, 43:1, John 10:30)

**THREE**

Person (Hypostasis), Name, Deed

(Matt 28:19, 1 Cor 12:4-6, Romans 14:17)

# ባህርይና አካላት
## (Essence and Persons)

- "**ባህርይ**" ማለት **ምንነትን** የሚያሳይ ሲሆን የእግዚአብሔር ባህርይ የሚባለውም ሰው ተመራምሮ የማይደርስበት የመለኮቱ ባህርይ ነው፡፡

- "**አካል**" የምንለው ደግሞ **ማንነትን** የሚገልጽ ሲሆን ሦስቱ አካላት አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ናቸው፡፡

- "**Nature**" is **what** God is:"What God is in His nature and essence that no human person has ever discovered or ever will discover."

- "**Person**" is **who** God is: "When I say God, I mean Father, Son and Holy Spirit."

**ምስጢረ ሥላሴን ተመራምሬ እደርስበታለሁ የሚል አዕምሮውን ያጣል፡፡ አልፈልግም ብሎ የካደው ደግሞ ነፍሱን ያጣታል፡፡**

**He who has tried to understand the mystery fully will lose his mind; but he who would deny the Trinity will lose his soul.**

**(Augustine (Western St)**

# በግብር ሦስትነቱ
## (Deeds/Relation)

**አብ**: ወላዲ (አባት)፣ አሥራፂ
- ❖ አይወለድም፣ አይሰርፅም

**ወልድ**: ተወላዲ (ልጅ)
- ❖አይወልድም፣ አያሰርፅም፣ አይሰርጽም

*(ምሳ 8፡23-25 ማቴ 3፡17 ማቴ 17፡5 ዮሐ 1፡34)*

**መንፈስ ቅዱስ**: ሠራፂ (የሠረፀ)
- ❖አይወለድም፣ አይወልድም፣ አያሰርፅም

*አይቀዳደሙም፣ አይበላለጡም፣ አይለያዩም*

**The Father**: Eternally begets the Son, Eternally gives forth the Holy Spirit
- ❖The unbegotten, never proceeds

**The Son**: Begotten of the Father
- ❖Never begets, never gives forth the holy spirit, never proceeds

**The Holy Spirit**: Proceeds from the Father
- ❖ Never begets, unbegotten, never gives forth

*Co-equal, co-eternal and co-substantial*

# የአካል ሦስትነት
## (Three Persons)

- ለአብ ፍጹም አካል፣ ፍጹም መልክ፣ ፍጹም ገጽ አለው፡፡
- ለወልድም ፍጹም አካል፣ ፍጹም መልክ፣ ፍጹም ገጽ አለው ፡፡
- ለመንፈስ ቅዱስም ፍጹም አካል፣ ፍጹም መልክ፣ ፍጹም ገጽ አለው፡፡

አይከፋፈሉም፣ አይነጣጠሉም፣ ፍጹም አንድ ናቸው፡፡

- The Father has a perfect person, the Son has a perfect person, the Holy Spirit has a perfect person.
- There are three real, concrete and absolutely distinct Persons.
- Father, Son and Holy Spirit are three entirely distinct modes of existence.
- The three are not parts of the same person, nor three ways of manifestation to the world

Undivided, Inseparable, Perfectly united

# የስም ሦስትነት
# (Names of Persons)

- አብ፡ አባት፣ ልብ፣ ‘ከእኛ በላይ ያለው’ አምላክ
- ወልድ፡ ልጅ (የባሕርይ)፣ ቃል፣ ‘ከእኛ ጋር ያለው’ አምላክ፣ የእግዚአብሔር ክንዱ፣ የአብ ቀኝ እጅ
- መንፈስ ቅዱስ፡ እስትንፋስ፣ ‘በውስጣችን ያለው’ አምላክ፣ የአብ ምክሩ

- The Father: The Heart, God above or beyond us
- The Son: Son of God, His ‘Word’, or ‘Logos’, God with us
- The Holy Spirit: The ‘life’, or ‘breath’ of God, God within us

**ከአንዱም በቀር ማንም አምላክ እንደሌለ እናውቃለን። ፩ኛ ቆሮ 8፡4**

**There is no other God but one. 1 Corinthians 8:4**

# ምስጢረ ሥላሴ

ሥላሴ አንድ ሲሆኑ ሦስት፣ ሦስት ሲሆኑ አንድ ናቸው፡፡ አንድነቱ ሦስትነቱን ሳይጠቀልለው፣ ሦስትነቱ አንድነቱን ሳይከፋፍለው በሕልውና ተገናዝበው የሚኖሩ ናቸው፡፡

*Trinity is* ***Three in one and One in Three***

*The Trinity is not:*

*Three persons who together make one God*

*Three Gods joined together*

*Three properties of God*

# ምስጢረ ሥላሴ በብሉይ ኪዳን
# (Holy Trinity in the Old Testament)

- እግዚአብሔርም አለ፡- “ሰውን በመልካችን እንደምሳሌአችን **እንፍጠር”** ዘፍ.1-26 እዚህ ላይ “እግዚአብሔርም አለ” ሲል አንድነቱ፣ “እንፍጠር” ሲል ከአንድ በላይ መሆኑን ግሱ /ቃሉ/ ያመለክታል፡፡ ሦስት መሆኑን ግን በዚህ ቃለ አልወሰነም፡፡
- እግዚአብሔር አምላክ አለ፡- “እነሆ አዳም መልካሙንና ክፉውን ለማወቅ **ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ”** ዘፍ.3-22 በማለት ባለቤቱን አንቀጽን አንድ፣ አሳቡን ዝርዝሩን የብዙ አድርጎ ይናገራል፡፡ “እግዚአብሔር አለ” ሲል አንድነቱን፣ “ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ” ሲል ደግሞ ከአንድ በላይ መሆኑን ያመለክታል፡፡ በዚህ ቃል ግን ሦስትነቱን አልወሰነም፡፡
- እግዚአብሔርም አለ፡- “**ኑ እንውረድ** አንዱ የአንዱን ነገር እንዳይሰማው ቋንቋቸውን በዚያ እንደባልቀው፡፡” ዘፍ.11.6-8፡፡ “እግዚአብሔር አለ” ብሎ አንድነቱ፣ “ኑ እንውረድ” ብሎ ደግሞ ከአንድ በላይ መሆኑን ያመለክታል፡፡
- “በቀትርም ጊዜ እግዚአብሔር ለአብርሃም ተገለጠለት አብርሃም **ሦስት ሰዎችን** በፊቱ ቆመው አየ” ዘፍ.18.1-15 በማለት እግዚአብሔር አንድ መሆኑንና ሦስት አካል ያለው መሆኑን ወስኖ ያስረዳናል፡፡ ኢሳ 6፡3

- Genesis 1:26: “And God said, **Let us** make man in Our image, after Our likeness.” The plural number here indicates that God is not one Person.
- Genesis 3:22: “And the Lord God said, Behold, Adam is become as **one of us**, to know good and evil.” (These are the words of God before the banishment of our ancestors from Paradise.)
- Genesis 11:6-7: Prior to the confusion of tongues at the building of the tower of Babylon, the Lord said, “**Let us go** down, and there confound their language.”
- Genesis 18:1-3: “And the Lord appeared unto him at the oak of Mamre . . . And he (Abraham) lifted up his eyes and looked, and lo, **three men** stood by him. Isaiah 6:3

“በእግዚአብሔር ቃል ሰማዮች ጸኑ፥ ሠራዊታቸውም ሁሉ በአፉ እስትንፋስ፡፡”
መዝ 33:6

“By the word of the Lord the heavens were made,

And all the host of them by the breath of His mouth.” Psalm 33:6

# ምስጢረ ሥላሴ በሐዲስ ኪዳን

## (Holy Trinity in the New Testament)

**ብስራት**፡ “መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል፣ የልዑልም ኃይል ይጸልልሻል ስለዚህ ደግሞ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱሱ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል፡፡” ሉቃ.1-35፡፡

**ጥምቀት**፡ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተለየ አካሉ /ሰው ሆኖ/ በዮርዳኖስ ሲጠመቅ፣ አብ በደመና ሆኖ “የምወደው ልጄ ይህ ነው የሚላችሁን ስሙት” ሲል፣ መንፈስ ቅዱስ ደግሞ በራሱ ላይ በርግብ አምሳል ሲወርድበት ታይቶአል፡፡ /ማቴ.3.16-17፣ ማር.1:9-11፣ ሉቃ 3.21-22/

**በደብረ ታቦር**: ወልድ በተለየ አካሉ ሥጋን ተዋህዶ በደብረ ታቦር ተገኝቶ፣ አብ በሰማያት ሆኖ “በእርሱ ደስ የሚለኝ ልጄ እርሱ ነው፤ እርሱን ስሙት” የሚል ቃል ተናግሮ፣ መንፈስ ቅዱስ ደግሞ በደመና ጋርዷቸው ተለግጠዋል፡፡ ማቴ 17፡1-10

**Annunciation**: “Father sends the Holy Spirit upon the Blessed Virgin Mary, and she conceives of the eternal Son of God (Luke 1:35).

**Baptism**: The Father’s voice from heaven bears witness to the Son, saying, This is My beloved Son, in Whom I am well pleased; and at the same moment the Holy Spirit, in the form of a dove, descends from the Father and rests upon the Son (Matt. 3:16-17).

**Transfiguration**: The Father testifies from heaven, This is my beloved Son, in Whom I am well pleased; hear Him (Matt. 17:5), while as before the Spirit descends upon the Son, this time in the form of a cloud of light (Luke 9:34).

# ምስጢረ ሥላሴ በሐዲስ ኪዳን
## (Holy Trinity in the New Testament)

- “እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው … ደቀመዛሙርት አድርጓቸው ፡፡” ማቴ.28.19-20
- “የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ፣ የእግዚአብሔርም ፍቅር፣ የመንፈስ ቅዱስም ኅብረት ከሁላችሁ ጋር ይሁን ፡፡” 2ኛ ቆሮ.13-14፡፡
- “በሰማይ የሚመሰክሩ ሦስት ናቸው፡፡ እነርሱም አብ፣ ልጅም፣ መንፈስ ቅዱስም ናቸው፡፡ እነዚህ ሦስቱም አንድ ናቸው፡፡” 1ኛ.ዮሐ.5-7

- “Go therefore and make disciples of all the nations, baptizing them in the *name* of the Father and of the Son and of the Holy Spirit.” Matt. 28:19
- “The grace of the Lord Jesus Christ, and the love of God, and the communion of the Holy Spirit be with you all. Amen.” 2 Cor. 13:14
- “For there are three that bear witness in heaven: the Father, the Word, and the Holy Spirit, and these three are one.” 1 John 5:7

"እኔ ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ አጽናኝ እርሱም ከአብ የሚወጣ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ፥ እርሱ ስለ እኔ ይመሰክራል።" ዮሐ 15:26

---

*"But when the Comforter comes, whom I shall send to you from the Father, even the Spirit of truth, who proceeds from the Father, he will bear witness to me." John 15:26*

# ምሳሌዎች- ምሳሌ ዘየሐፅፅ

## Analogies: Truth # Analogy (1)

**ሥላሴ በፀሐይ ይመሰላሉ።**

ፀሐይ አንድ ሲሆን ሦስትነት አለው፡፡ ይህም ክበቡ ብርሃኑ፣ ሙቀቱ ነው፡፡ ክበቡ አብ፣ ብርሃኑ ወልድ፣ ሙቀቱ መንፈስ ቅዱስ ይመሰላሉ፡፡ «አብ ፀሐይ፣ ወልድ ፀሐይ፣ መንፈስ ቅዱስ ፀሐይ አሐዱ ውእቱ ፀሐየ ጽድቅ ዘላዕለ ኩሉ» እንዳለ /ቅዱስ አባ ሕርያቆስ/፡፡

**የሥላሴ አንድነትና ሦስትነት በሰው ምሳሌ ይገለጻል፡፡**

ሰው በነፍሱ ሦስትነት አለውና ነው፡፡ የኸውም ልብነት፣ ቃልነት፣ ሕይወትነት ነው፡፡ ስለዚህ በሰው ነፍስ በልብነቷ አብ፣ በቃልነቷ ወልድ፣ በሕይወትነቷ መንፈስ ቅዱስ ይመስላሉ፡፡ የነፍስ ልብነቷ፣ ቃልነቷን፣ ሕይወትነቷን ከራሷ ታስገኛለችና፡፡ ቃልና ሕይወት ከአንዱ ልብ ስለተገኙ በከዊን /በመሆን/ ልዩ እንደሆኑ በመናገርም ይለያሉ፡፡

**ሥላሴ በእሳት ይመሰላሉ፡፡**

እሳት አንድ ሲሆን ሦስትነት አለው፡፡ ይህም አካሉ፣ ብርሃኑ፣ ዋዕዩ /ሙቀቱ/ ነው፡፡ በአካሉ አብ፣ በብርሃኑ ወልድ፣ በዋዕዩ መንፈስ ቅዱስ ይመሰላሉ፡፡ «አብ እሳት ወልድ እሳት ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ ውእቱ እሳተ ሕይወት ዘእምአርያም፡፡» /አባ ሕርያቆስ/ «አምላክህ እግዚአብሔር የሚባላ እሳት ቀናተኛም አምላክ ነው፡፡» ዘዳ. 4-24፡፡

**The Sun**: It is written, “The Lord God is a sun…” (Ps 84:11) The sun has been used as an analogy for the Holy Trinity. The sun has ray and light. You cannot separate the light from the ray and you cannot separate either from the sun

**Man**: Man who is created “in the image of God” (Gen 1:26) is one of the best analogies for the Truth of the Holy Trinity. Man is of one humanity possessing a mind and a spirit. Personality, mind, and spirit comprise just one human being.

**The Fire**: It is written, “Our God is a consuming fire” (Heb 12:29). Fire can be used as an analogy for the Holy Trinity for fire generates light and heat. Nevertheless, the flame, its light and its heat are one entity. From the moment the flame begins, from that moment light and heat also begin.

# ምሳሌዎች - ምሳሌ ዘየሐፅፅ

## Analogies: Truth # Analogy (2)

### የባህር ከዊን (Sea Triad)

- ባህር አንድ ባህር ሲሆን ሦስት ከዊን አለው:: ይህም ስፍሐት (Sphere)፣ ርጥበት (Moisture) እና እንቅስቃሴ (Tide) ነው::
- በስፍሐቱ አብ፣ በርጥበቱ ወልድ፣ በእንቅስቃሴው መንፈስ ቅዱስ ይመሰላሉ::
- ሰው ከባህር ገብቶ ዋኝቶ ሲወጣ በአካሉ ላይ ርጥበት ይገኛል እንጂ ስፍሐትና እንቅስቀሴ አይገኝም:: ወልድም በቃልነቱ ከዊን ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ሳይለይ በተለየ አካሉ ሰው በሆነ ጊዜ በመለኮት አንድ ስለሆነ አብና መንፈስ ቅዱስ ሥጋ ለበሱ አያሰኝም::
- የሁሉ መገኛ አብን ነፋስ በሚያማታት ባህር ባለች ውኃ እንደመሰሉት እወቅ:: በሁሉ ዘንድ የሚመሰገን ወልድንም በውኃ ርጥበት እንደመሰሉት በሁሉ ዘንድ የሚመሰገን መንፈስ ቅዱስንም በውኃ ባለ ባህር እንቅስቃሴ ይመሰላል::

### The Spring of Water (*A separate analogy*)

- "The wellspring of wisdom is a flowing brook" (Prov 18:4)
- The well (fountain), spring and stream (river) have been used as an analogy for the Holy Trinity.
- Just as the spring and the stream produced from a well are not separate.
- There are in fact three visible objects and three names.
- They all have the same water.

# ምስጢረ ሥላሴ ላይ የሚነሱ የስህተት ትምህርቶች- መለዋወጥ

## Trinitarian heresies: Modalism/Seballianism

- አንድ እግዚአብሔር አለ፡፡ እርሱም ራሱን በተለያየ መንገድ ይገልጻል፡፡
- አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ የሚባሉት አካላት ሳይሆኑ ራሱን የገለጠባቸው መንገዶች ናቸው፡፡
- እግዚአብሔር አንድ ጊዜ አብ ሌላ ገዜ ወልድ ሌላ ጊዜ ደግሞ መንፈስ ቅዱስ ሆኖ ይገለጣል፡፡
- ይህም ውኃ ፈሳሽ፣ በረዶ፣ እንፋሎት እንደሚሆነው ነው፡፡
- *እኔ እግዚአብሔር አልለወጥም:: ሚል 3፡6*

- There is but one God who simply reveals Himself through three different modes, or roles.
- Father, the Son, and the Holy Spirit are not distinct personalities, but different modes of God's self-revelation.
- There is only one God, but that this one God reveals himself in different ways and different forms - sometimes as Father, sometimes as Son, sometimes as Holy Spirit.
- The Trinity is like water because water comes in three forms - ice, water, steam. This is Modalism because these are three states or modes of the substance water.
- *For I am the Lord, I do not change. Malachi 6:3*

# ምስጢረ ሥላሴ ላይ የሚነሱ የስህተት ትምህርቶች - ሦስት አማልክት

## Trinitarian heresies: Tri-theism

- አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ሦስት አማልክት ናቸው፡፡
- ልዩ በሆነ መንገድ የተጣመሩ አማልክት ናቸው፡፡
- ሦስት አካላት የሚለውን በትክክል ባለመረዳት የሚመጣ ነው፡፡
- *ነገር ግን ሥላሴ የተለያዩ/የተነጣጠሉ/ አይደሉም፡፡*

- Father, Son and Holy Spirit are three independent divine beings; three separate gods who are linked together in some special way.
- People often make this mistake because they misunderstand the use of the word "persons" in defining the Trinity.
- *But Trinity does not mean that Father, Son and Holy Spirit are three separate personalities.*

# ምስጢረ ሥላሴ ላይ የሚነሱ የስህተት ትምህርቶች - መከፋፈል
## Trinitarian heresies: Partialism

- አብ ወልድና መንፈስ ቅዱስ አንድ ላይ ሲሆኑ አምላክ ይሆናሉ፡፡
- እያንዳንዳቸው የአምላክ ክፍል ናቸው እንጂ ሙሉ አምላክ አይደሉም፡፡
- ሦስቱ በአንድ ላይ ሲሆኑ ብቻ ሙሉ አምላክ ይሆናሉ፡፡
- *ሥላሴ ግን አይከፋፈሉም፡፡*

- Father, Son and Holy Spirit together make up God.
- This would suggest that each of the persons of the Trinity is only part God.

.

- The three only becoming fully God when they are together.
- *But Trinity means there is exactly one God; There are three really distinct Persons - Father, Son, and Holy Spirit. Each of the Persons is God.*

# ምስጢረ ሥላሴ ላይ የሚነሱ የስህተት ትምህርቶች - አርዮሳዊነት
## Trinitarian heresies: Arianism

- የወልድን ፍጹም አምላክነት የሚክድ ትምህርት ነው፡፡
- ወልድ በአብ በልዕልና የተፈጠረ ነው ይላል፡፡ ፈጥሮ ፈጠረበት ይላል፡፡
- ወልድ ያልነበረበት ጊዜ ነበር የሚል ነው፡፡
- በኒቅያ ጉባዔ የተወገዘ ትምህርት ነው፡፡
- **ቃልም እግዚአብሔር ነበረ።** *ዮሐ 1:1*

- "There was a time when the Son of God was not."
- Arius insisted that Son of God was not truly God;
- Arius said the Son was merely the highest of created beings, and in that sense we could call him a god.
- This belief is virtually identical to the present day heresy of the Jehovah's Witness.
- Denounced at Council of Nicea (325 AD).
- **The Word was God.** *John 1:1*

# ምስጢረ ሥላሴ ላይ የሚነሱ የስህተት ትምህርቶች - መቅዶንዮሳዊነት
## Trinitarian heresies: Mecedonianism

- የመንፈስ ቅዱስን ፍጹም አምላክነት የካደ ትምህርት ነው፡፡
- መንፈስ ቅዱስ ፍጡር (ሕፁፅ) ነው ይላል፡፡ ከአብና ከወልድም ያንሳል ይላል፡፡
- እኛ ግን በሦስቱ አካላት መበላለጥ የለም ብለን እናምናለን፡፡
- የመቅዶንዮስ ትምህርት በቁስጥንጥንያ ጉባዔ የተወገዘ ትምህርት ነው፡፡
- *መንፈስ ቅዱስ ፍጹም አምላክ ነው፡፡ ዮሐ 3፡5 ሐዋ 5፡5*

- A heresy that denied the full personality and divinity of the Holy Spirit.
- According to this heresy, the Holy Spirit was created by the Son and was thus subordinate to the Father and the Son.
- But God is one in essence but three in Person—Father, Son, and Holy Spirit, who are distinct and **equal**.
- Denounced at Council of Constantinople (381 AD).
- *The Holy Spirit is God. John 3:5 Acts 5:5*

# ምስጢረ ሥላሴ ላይ የሚነሱ የስህተት ትምህርቶች - ሁለት ሥርጸት
## Trinitarian heresies: Dual procession

- መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ ይሰርፃል የሚል የስህተት ትምህርት ነው።

- የኒቅያ ጉባዔ ድንጋጌ ላይ ከጊዜ በኋላ የተጨመረ ነው።

- በጥንታዊያን አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ያልነበረ ምዕራባዊያኑ ያስገቡት ነው።

- ከምስጢረ ሥላሴ ጋር ይጣረሳል።

- **Filioque clause:** The Holy Spirit as proceeding from both the Father and the Son, (and not from the Father only).
- This was gradually inserted into the Nicene Creed so that it stated that the Holy Spirit proceeds not from the God the Father alone, as the early Church Fathers believed, but from *both God the Father and God the Son*.
- This idea detracts from the separate character of each person of the Trinity, and confuses their relationships

“‘አብ አምላክ ነው፣ ወልድም አምላክ ነው፤
መንፈስ ቅዱስም አምላክ ነው፣ ነገር ግን ሦስት አማልክት አይባሉም፤
አንድ አምላክ ነው እንጂ::’’ *ቅዱስ አትናቴዎስ*

“The Father is God, the Son is God, the Holy Spirit is God. They are called one God but not three Gods.”

*(Apostolic Athanasius Faith of the Fathers Ch. 24 Part 4 Verse 4)*

“ምንም እንኳን ሥላሴን በስም፣ በአካል በግብር ሦስት ናቸው ብንልም ሦስቱ በባህርይ፣ በመለኮት፣ በህልውና፣ በፈቃድ አንድ ናቸው፡፡ አንድ አምላክ እንጂ ሦስት አማልክት አንልም፡፡ አብ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ፍጹም አካል ፍጹም ገጽ አላቸው፡፡ ነገር ግን በህልውና አንድ ናቸው፡፡”

“Even though we say the Trinity are three in name, in deed and in person; the three are one in essence, in divinity, in existence and in will; we do not mean three Gods but one God. While the Father and the Son and the Holy Spirit exist in their own perfect person, they are one in existence.”

*(Faith of the Father's Ch. 40 Verse 4:6)*